# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ግንቦት 2/2000

## ለሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማህበራትና ተቋሞች

## አስቸኳይ መልዕክት

ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ገጥመዋት ካሉ ፈተናዎች ሁሉ በዛሬው ጊዜ የከፋ ፈተና ከፊቷ ተደቅኖ ህልውናዋንና ክብሯን ለአደጋ ስለጣለው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በነቂስ ሆነ በድርጅት ደረጃ፣ በማህበርና በተቋም ደረጃ ሀገር ተደፈረች ብሎ በጋራ መነሳት አለበት። የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ለምና ማዕድን አለበት የተባለውን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቷል።
በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገሩን መደፈር በመቃወም በጋራ ተቃውሞውን ማሰማት አለበት። በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ መሬት ለባዕድ ተሰጠ ፤ ዜጎች በባዕድ ጦር ተጠቁ ብለን በጋራ ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማት አለብን። በዚህም መሰረት ኢሕአፓ ለሁሉም ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች፣ ተቋሞችና ማህበራት ሁሉ ጥሪውን ያቀርባል። ይህ ጥሪ የትግል ነው። በሱዳን የተወሰደው መሬት የጎንደር ወይም የጋምቤላ ሳይሆን የኢትዮጵያ ነው። ወረራው ሁላችንንም ይመለከታል፣ የተደፈርነው ሁላችን ነን፣ኢትዮጵያ ናት። ኢሕአፓ ደግሞ በጎንደር ሕዝብታ ቅፎ የታገለ ነውና በዚያ አካበቢ ሕዝብ ላይ የሚደርስ በደልን አላየሁም አልሰማሁም ማለቱ የሚከብደው ነው። ከዚህ ቀደም ሱዳን የኢትዮጵያን መሬት ሊደፍር ሲነሳ ኢሕአፓ ከጎንደርና ጎጃም ሕዝብ ጋር ሆኖ በቆራጥነት አክሽፎታል። ዛሬምቢሆን ይህን የወያኔና የሱዳን ድፍረት በቸልተኝነት ልናየው የምንችል ባለመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛን ተቃውሞ በጋራ ለማስተጋባት መተባበር አለብን ብሎ ኢሕአፓ ያምናል።
<u>ስለዚህም ለሁሉም ሀገር ወዳድ ድርጅት፥ ተቋማትና ማህበራት የሚያስተላልፈው ጥሪ እንገናኝ፣ እንወያይና የጋራ ተቃውሞ እናዘጋጅ የሚል ነው።</u> በዚህም መሰረት ሁሉም
ፀረ ወያኔ ድርጅቶች፥ ማህበራት፥ ተቋሞች፥...ወዘተ ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት ፈጥረው በጋራ የተቃውሞ እንቅስቃሴን ለማዘጋጀት እንዲጥሩ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርጋል። ሀገር ሲወረር ሲደፈር ጥቃቱ የሁላችን ነውና ሁሉም ዜጋ ተደፈርን ብሎ መነሳት መቃወም አለበት። ኢሕአፓ ከሁሉ ድርጅት፥ ማህበርና ተቋም መልዕክት ይጠብቃል።

ሀገር ሲደፈርና ሲወረር ዝምታ ወንጀል ነው።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France